ማሕበር ተጋሩ ሰሜን ኣሜሪካ (ማ.ተ.ሰ.ኣ)

**UNION OF TIGREANS IN NORTH AMERICA (UTNA)**

P.O.BOX 73736
Washington, DC 20056
utnaoffice@gmail.com

Tel. (202) 862-4367
Fax. (202) 265-8703
www.utna.org

ቀን፦ ኤፕሪል 02፣ 2018

## የመልካም ምኞት መግለጫ
## ከትግራይ ተወላጆች ማሕበር በሰሜን አሜሪካ

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው ልዩ ስብሰባው፣ አብይ አሕመድ ዓሊ (ዶ/ር) የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስቴር አድርጎ በመሰየሙ የተሰማንን ደስታ በማሕበራችን አመራር እና አባላት ስም ለመግለጽ እንወዳለን። ይህ ሂደት ከብዙ መስዋዕትነት እና የተራዘመ መራራ ትግል በሀገራችን ሕገ መንግስታዊ ፌደራላዊ ስርዓት መመስረት ተከትሎ የመጣ እና በአዲሲቷ ኢትዮጵያ ስልጣን ከህዝብ ድምጽ ብቻ የሚመነጭበት፤ ሃይማኖት እና ብሔር ሳይለይ ሁሉም ኢትዮጵያዊያን በእኩል በሀገር ጉዳይ የሚሳተፉበት እና ሀገር የሚመሩበት፤ እንዲሁም በአካባቢያቸው ራሳቸውን በራሳቸው ለማስተዳደር የመቻላቸው መብት አንዱ መገለጫ ነው። የዛሬው የዶ/ር አብይ አሕመድ ዓሊ ሲመትም የዚሁ ላለፉት 27 ዓመታት ሲተገበር የመጣ ዲሞክራሲያዊ ሂደት አንድ አካል ነው። ማሕበራችን አሁን በአዲሲቷ ኢትዮጵያ እውን የኾነውን ስርዓት ለማምጣት እና ለመትከል ከትጥቅ ትግሉ ዘመን ጀምሮ መስዋዕት የከፈለ አንጋፋ ማሕበር እንደ መኾኑ፣ በዚህ ሰላማዊ እና ዲሞክራሲያዊ የስልጣን ሽግግር ልዩ ኩራት እና ክብር ይሰማዋል።

ሀገራችን ኢትዮጵያ ባለፉት 16 ዓመታት በኢኮኖሚው ዘርፍ ያስመዘገበችው መጠነ ሰፊ እምርታ ማሕበራችን ይረዳል። ላለፉት ሶስት ዓመታት ሀገራችን ውስጥ የተከሰተው የዜጎች በማንነታቸው ምክንያት ተለይትው የመፈናቀል፣ የመሞት ንብረት የመውደም እና ሀገር ከስርዓት ውጭ ኾና፣ ሰላሟ ተናግቶ፣ የህዝብ እና የሀገር አንጡራ ሀብት የጠፋባቸው ዓመታት ነበሩ። ማሕበራችን በዚህ ክስተት በእጅጉ አዝኗል። ሀገራችን በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ባለችበት፣ ዶ/ር አብይ አሕመድ ወደ ጠቅላይ ሚኒስቴርነት መምጣታቸው ይታወቃል። ስለዚህም አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስቴር፣ እንዲሁም አጠቃላይ መንግስት፣ ይህንን የሀገራችን የኢኮኖሚ ግስጋሴ ላይ ጥቁር ጠባሳ ያሳረፈ እና አጠቃላይ የሀገራችን ገጽታ ያበላሸ ሀገራዊ ቀውስ እንዲያበቃ፣ ዜጎች በሀገራቸው በሰላም ወጥተው የሚገቡበት፣ በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል በነጻነት የመኖር፣ የመስራት እና ሀብት የማፍራት ሕገ መንግስታዊ መብታቸው የሚከበርበት ስርዓት እንዲተገበር ሊሰሩ እንደሚገባቸው በአጽንኦት ለመግለጽ እንወዳለን።

አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስቴራችን ዶ/ር አብይ አሕመድ የመጀመርያው የኦሮሞ ተወላጅ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስቴር መኾናቸው ስናስብ፣ ለብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች እኩልነት የከፈልነው መስዋዕትነት ፍሬ ማፍራቱን እና መስዋዕትነታችን ከቡር መኾኑን እንደ ማሕበር እንረዳለን። ሰላም ወዳድ የኾነው የኦሮሞ ህዝብ በዲሞክራሲያዊ የገዳ ስርዓት አንጾ ያሳደጋቸው ዶ/ር አብይ አሕመድን

ለጠቅላይ ሚኒስቴርነት በማበርከቱ፣ እንዲሁም መሪው ድርጅቱ ኢህአዴግ በድርጅታዊ ስነ ምግባር ኮትኩቶ ያበቃቸው ወጣት ተተኪ መሪ በዲሞክራሲያዊ መንገድ የድርጅቱ ሊቀ መንበር አድርጎ መምረጡ እጅግ የሚያስመሰግናቸው ነው ብለን እናምናለን።

በመጨረሻም ለአዲሱ ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶ/ር አብይ አሕመድ ዓሊ መልካም የስራ ዘመን እየተመኘን፣ ቀጣይ የመሪነት ጉዟቸው ስኬታማ እንዲኾን በሀገራዊ ጉዳዮች፣ በህዝብ ደህንነት እና ጥቅም እንደ ካሁን በፊቱ በጎ ለውጥ ሲኖር እያበረታታን ጉደለት ሲፈጸም ደግሞ እየታገልን በጋራ ተባብረን እንደምንሰራ ልንገልጽ እንወዳለን።

ሰላም እና ብልጽግና ለኢትዮጵያ!

የኢትዮጵያ ህዝቦች እኩልነት፣ ትብብር እና ዲሞክራሲያዊ አንድነት ይጠንክር!

የትግራይ ተወላጆች ማሕበር በሰሜን አሜሪካ
ማእከላዊ ጽ/ቤት
ዋሽንግተን፣ ዲሲ